*የሰ/መ/ቁ. 64734*

*ሰኔ 16 ቀን 2003 ዓ.ም*

**ዳኞች**:- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**:- ካንትሪ ክለብ ዴቨሎፐር የረር ቪው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት - ነገረ ፈጅ ታማኝ የበነ - ቀረበ

**ተጠሪዎች**:- 1. አቶ በቀለ ለማ - ቀረቡ

2. አቶ ተሾመ አጫሉ - ቀረቡ

3. አቶ ባህሩ አበራ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ሲሆን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበው በአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሽነት ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በተከሣሽ ድርጅት ውስጥ በአናጢነት ሙያ ተቀጥረን 1ኛ ከሣሽ በቀን ብር 36 ፣ 2ኛ ከሣሽ ብር 39 እና 3 ከሣሽ ብር 20 እየተከፈለ በመስራት ላይ እያለን ነሐሴ 17 ቀን 2002 ዓ.ም ያለአግባብ ከስራ ላይ ያሰናበተን ስለሆነ ወደ ምድብ ስራችን እንድንመለስ ወደ ስራ የማይመልሰን ከሆነ ደግሞ በህጉ መሠረት ሊከፍለን የሚገባውን ክፍያዎች እንዲከፍለን የሚል ነው፡፡ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ መጥሪያ ደርሷቸው በሰጡት መልስ ከሣሾች ከስራ የተሰናበቱት ድርጅቱ ከመዝገብ ቤት የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ አንቀበልም በማለታቸው በህብረት ስምምነቱ መሠረት ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ካከራከረ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክር በመስማት የተከሣሽ ምስክሮች ከመዝገብ ቤት ወጪ ሆኖ ለከሣሾች የተጻፈውን ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ አንቀበልም ማለታቸውን አረጋግጫለሁ በሌላ በኩል የተከሣሾች ምስክሮች ቃል እርስ በርስ የሚቃረን በመሆኑ ማስተባበል አልቻሉም፤ ከድርጅቱ መዝገብ ቤት ተጽፎ የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ አልቀበልም ማለት ደግሞ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 58/10/ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብት የሚችል በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የአሁን አመልካች እየሰጠ የነበረው ማስጠንቀቂያ ሣይሆን ቀደሞ በቅጥር ውላቸው

ውስጥ የተጠቀሰውን በቀን 5 ካ.ሜ የአሁን ተጠሪዎች ለመስራት የገቡትን ግዴታ ወደ 10 ካ.ሜ. ለማሻሻል የተደረገ በመሆኑ የአሁን አመልካች በራሱ ተነሳሽነት በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን የስራ ውል ስምምነት መጣሱን እንጂ በጥፋት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ባለመሆኑ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሯል፡፡ የተጠየቀውን ክፍያ በተመለከተም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ፣ የስራ ስንብት እና የካሣ ክፍያ እንዲከፍላቸው አመልካች ኃላፊነት እንዳለበት ወስኗል፡፡ አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በቀን 23-5-03 ዓ.ም በነገረፈጅ በኩል በተጻፈ 4 ገጽ አቤቱታ ፍሬ ሃሣብ ከድርጅቱ መዝገብ ቤት ወጪ ሆኖ ለሰራተኞች የሚሰጠውን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ አልቀበልም ማለት በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 58/10/ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ሆኖ እያለ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይሄንን በማለፍ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት የቀረበ ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ታዘው የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ ፍሬ ሃሣብ ያቀረብኳቸው የሰው ምስክሮች የተባለው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተሰጠ ለተባለበት ያልነበርና እንቢ ያላልን መሆኑን መስክሮልናል ፤ አንፈርምም ያልነው ደግሞ ቀድሞ የተስማማንበት የስራ ውል በቀን 5 ካ.ሜ ሆኖ እያለ አሁን ደግሞ 10 ካ.ሜ እንድንሰራ ያዘዘን በመሆኑ ከአቅማችን በላይ በመሆኑ እምቢ ማለታችን እንጂ በጥፋተኝነት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ባለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የቀረቡትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት በህጋዊ መንገድ ወይስ በህገ-ወጥ መንገድ ነው? በሚል ጭብጥ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27 ስር ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ የሚችሉ ጥፋቶችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ 5 አንቀጽ 27/1/ ስር ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰብቱ የሚችሉትን ጥፋቶች በህብረት ስምምነታቸው መደንገግ እንደሚችሉና በዚሁ መሠረት በድርጅቱ ውስጥ ስራ ላይ ያለው የህብረት ስምምነት አንቀጽ 58/10/ ከመዝገብ ቤት የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ አልቀበልም ማለት እንደ አንድ በቂ ምክንያት የተቀመጠ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የአሁን አመልካችም የሚከራከሩት ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ይሄ የህብረት ስምምነት አንቀጽ እንደሆነና የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ያለመቀበል በራሱ ከስራ ለማሰናበት በቂ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች የሚከራከሩት የተጻፈው ደብዳቤ ባጠፋነው ጥፋት የተሰጠ ሣይሆን በስራ ውላችን ውስጥ የተስማማንበትን በቀን 5 ካ.ሜ ለመስራት ውል የገባንበትን በመለወጥ በቀን 10 ካ.ሜ እንድንሰራ የታዘዘንበት ነው በማለት የተጠቀሰው የህግ አንቀጽ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት እንደሌለው ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመረምር የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/1/ መግቢያን በምናይበት ጊዜ በሌላ አኳኋን በህብረት ስምምነቱ የተካተተ ካልሆነ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ የሚችሉ ነገሮች በዚሁ አንቀጽ ስር የተዘረዘሩት ብቻ እንደሆኑ ያመለክታል፡፡ ለህብረት ስምምነቱ መውጣት መሠረት የሆነው የአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/ተ/ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ ይችላሉ ተብለው በህብረት ስምምነት የሚደነገጉት ሌሎች ጥፋቶች እንደሆነ ያመለክታል፡፡

ይሄ ማለት ደግሞ በህብረት ስምምነት እንደምክንያት ሊደነገጉ የሚችሉት ነገሮች ጥፋትን መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት ያመለክታል፡፡

አሁን ለተጠሪዎች ከስራ መሰናበት መሠረት የሆነውን የህብረት ስምምነት አንቀጽ 58 ስንመለከትም የአንቀፁ ርዕስ ከስራ የሚያሰናብቱ ከባድ ጥፋቶች በሚል ከመደንገጉም በላይ የዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 10 በተያያዘ መልኩ "ድርጅቱ ከመዝገብ ቤት የሚሰጠውን የማስጠንቀቂያ ወረቀት አልቀበልም ካለ" በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሄንን ሁሉ አንድ ላይ ጠቅለል አድርገን ስንመለከት የስራ ስንብቱ የሰራተኛውን ጥፋት መሠረት ያደረገና የሚሰጠውም ማስጠንቀቂያ ጥፋትን መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት ያመለክታል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች እንዲቀበሉ የታዘዙትን ደብዳቤ አንቀበልም ማለታቸው በመጀመሪያ ጉዳዩን ባየው ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑ ቢታመንበትም እየተሰጣቸው ያለው ደብዳቤ ከላይ እንደተብራራው የህግ ድንጋጌዎች ጥፋትን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም ከሚለው አኳያ መታየት አለበት፡፡

በዚህ መሠረት ተጠሪዎች እንዲቀበሉ እየታዘዙ ያሉት ቀድሞ በስራ ውላቸው ውስጥ በቀን ተጠሪዎች 5 ካ.ሜ ለመስራት የተስማሙበትን አመልካች በቀን 10 ካ.ሜ እንዲሰሩ የጻፈባቸውን ደብዳቤ ስለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው በመሆኑ የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ደግሞ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ /ሀ/ እና በአዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 10 መሠረት መሠረታዊ የህግ ስህተት ሲኖር ማረም በመሆኑ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሠረቱ አመልካችም የሚከራከረው የተጻፈው የደብዳቤ ይዘት ከዚህ የተለየ ስለመሆኑ ሣይሆን ደብዳቤውን ያለመቀበላቸው ብቻ ከስራ ለማባረር በቂ ነው ከሚለው ነጥብ አኳያ በመሆኑ አልፈነዋል፡፡

የተጻፈባቸው ደብዳቤ ይዘት ከላይ የተመለከተው በመሆኑ አመልካችም ተጠሪዎች ሲቀጠሩ የነበረው ውል በቀን 5 ካ.ሜ ለመስራት እንደተስማሙ ባላስተባበሉበት በራሱ ተነሣሽነት በውላቸው ውስጥ የተቀመጠውን የቀን የስራ መጠን በመተላለፍ በቀን 10 ካ.ሜ እንዲሰሩ ማለቱና ቀድሞ የነበረውን የስራ ውል የሚያስቀይር ጉዳይ መኖሩን እንኳ ባላስረዳበት በራሱ መጻፍና አንቀበልም ብሏል በማለት ከስራ ማሰናበቱ ከተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ/ቁ. 99340 በቀን 09-05-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ተጠሪዎችን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበተው ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ተያያዥ ክፍያዎች ለተጠሪዎች እንዲፈጸሙ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በቀን 01-06-2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

እ.ከ　　　　　　　　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት